# ኢትዮጵያና የዓለም ሁኔታ ምን ይመስላል?

ከተንሳይት በቃና

በአሁኑ ግዜ የዓለምን ሁኔታ ስንመለከት ሩሲያ፣ ቻይና፣ ኢራንና ሶሪያ በአንድ ወገን ሲሆኑ በሌላ ወገን ደግሞ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ሌሎች የኔቶ አባል አገራትና እስራኤልና ሰውዲ ዓረቢያ አንድ ላይ በመሆን ሶሪያን፣ኢራን፣ የመንና ሰሜን ኮሪያ ላይ ጥቃት በማካሄድና ለማካሄድ የተለያዩ በጦር ለማጥቃት የሚያስችላቸውን ምክንያት እንደ ኢራቁ ወረራ ወቅት ዛሬም በተለይ ምዕራባውያን የእውሸት መደርደርና የተካኑበትን ፕሮፓጋንዳ እያካሄዱ ይገኛሉ። ለምሳሌ የሶሪያ መንግስት ተገቢ ያለሆነ ኬሚካል ለመጠቀምና የራሱን ሕዝብ ለመግደል እንደተዘጋጀ እውሸት የሆነ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት፣ ምዕራባውያን እራሳቸው አክራሪ በገንዘብ የተገዙ የገዳዮች ግሩፖችን ኬሚካሉን በመስጠት ሶሪያ ውስጥ ጸረ የሶሪያ ሕዝብ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በሰውር አየሰሩ መሆናቸው በተደጋጋሚ ተጋልጧል። ሌላው በጣም አስቂኝ የሆነው ደግሞ የእንግሊዟ ፕራይም ሚኒስቴር ሜይ የሩሲያና የእንግሊዝ ሰላይ የነበረው ለንደን ውስጥ የሚኖረውንና ልጁን ሩሲያ በሰራቸው መርዝ እንደተመረዘ አድርጋ ዓይኗን በጨው አጥባ ያለምንም ማስረጃ በማቀረብ፣ የእዚህ የእሷ እውሸት ተባባሪዎችን በመሆን የአውሮፓ ሕብረት አገሮች፣ ካናዳ፣ ዩክሬን፣ አውስትራሊያና አሜሪካ የሩሲያ ዲፕሎማቶችን ከአገራቸው አስወጥተዋል። በአውሮፓ ውስጥ ይህንን የእንግሊዝን ፕራይም ሚንሲተር ሜይ እውሸት አልቀበልም በማለት ትክክለኛውን መንገድ የተከተለች አገር ብትኖር አውስትሪያ ናት።ሩሲያም በበኩላ የእንግሊዝንና የአሜሪካን ዲፕሎማቶችን በድምሩ 83 ከአገሯ እንዲወጡ ወስናለች። የቱርክ መንግስት ጦሩን በሶሪያ ውስጥ በማስገባት ኩርዶችንና ሌሎች የማይፈልጋቸውን በቦምብ አየደበደበች ትገኛለች።ሩሲያ በሶሪያ ላይ አሜሪካ የቦምብ ውርጅቢኝ ለማውረድ እቅዷ እንደነበረ ሩሲያ ስለደረሰችበት፣ ሩሲያ ሶርያን የማጥቃት እርምጃ ከተወሰደ ሩሲያ አጸፋውን እንደምትመልስ አስጠንቅቃለች። የአሜሪካን መንግስትና የሳውድ ዓረቢያ መንግስት ግንኙነት የሳውድ ዓረቢያ ላይ የአሜሪካ መንግስት ትኩረት በማድረግ ፕሬዚደንት ትራምፕ የመጀመሪያውን ጉብኝት በማድረግና በብዙ ዶላሮች የሚተመኑ የአሜሪካ ጦር መሳሪያዎችን ሳውድ ዓረቢያ እንድትገዛ ስምምነት ተደርሷል።በሁለተኛ ደረጃ የክሊንተን፣ ቡሽና ኦባማ መንግስታትን አሸባሪዎች በፋይናንስ ትረዳ የነበረችው ሳውድ ዓረቢያ ስለነበረች፣ የሳውዲ ዓረቢያ ባለስልጣናትና ሃብታሞች በፕሬዚደንት ትራምፕ መንግስት ትብብር በቁጥጥር ስር እንዲሆኑና ገንዘባቸውም በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደርጓል።ከዚህ በቁጥጥር ስር ከዋለው ገንዘብ ውስጥ በብዙ ዶላሮች የሚቆጠር ገንዝብ የሳውድ ዓረቢያ መንግስት ኢንቬስት ለማድረግ የሳውድ ዓረቢያ መሪ ለፕሬዚደንት ትራምፕ አረጋግጧል። የዲፕ-ስቴትና የጸረ-ዲፕ ስቴት እንቅስቃሴዎች ዲፕ-ስቴት የሚባለው ግሩፕ በዓለም ውስጥ ያሉ ጥቂት ግሩፖች የዓለምን ሕዝብ ቁጥር አሁን ካለበት 7 ቢሊዮን ወደ ግማሽ ሚሊዮን ለመቀነስ፣ ሮቦታዎችን በማዘጋጀት ለሚፈልጉት ሰራዎች ጥቅም ላይ ለማዋል፣ የዓለምን ሕዝብ ቁጥር በተመረዘ ምግብ፣ መሃን በሚያደርግ ምግብ፣ መሃን በሚያደርግ ክትባቶች፣ በሽታ በሚያሲዙ ጨረሮችን በመጠቀም፣ ቫይረሶችን በማሰራጨት፣ በጦርነቶች፣ ህጻናትን ለሰይጣናዊ አምልኮት መስዋዕት

በማድረግ፣ በአንዛኸ እጽ በመጠቀም፣ ማይንድ ኮንትሮል በተባለው አሰራር የስለላ ድርጅቶች የሰውን አእምሮ በመቆጣጠር ግለሰቡ የማይፈልገውን ድርጊት እንዲፈጽምና ከዚያም ድርጊቱን እንዲረሳ በማድረግ የተለያዩ ሽብሮችን በፈለጉበት አካባቢ በማካሄድ፣. . . ወዘተ የሚንቀሳቀሱ ግሩፐች ናቸው።እነዚህ ግሩፖች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት የፌዴሬላ ሪዝርቭ ባንክ በአሜሪካ፣ ባንክ ኦፍ ኢንግላንድ፣ ባንክ ኦፍ ሲዊዝና የቫቲካን ከፍተኛ ስልጣን ያላቸውንና የእንግሊዝ፣ የአሜሪካን የእስራኤል ስለላ ድርጅቶች፣ የሚሊታሪ መሳሪያዎች አምራቶች ኩባንያዎች፣ የግል ተቀጣሪ ነፍሰ ገዳዮች፣ ከፍተኛ ጀኔራሎ፣ የህክምና ዶክቶሮች፣ የፖሊስ ባለስልጣናት፣ ከፍተና ፍርድ ቤቶች፣. . . ወዘተ የሚያጠቃልል ነው። በአሜሪካ ውስጥ ፕሬዚደንት ትራምፕ ጸረ ዲፕ-ስቴት እንቅስቃሴዎችን እያካሄደ እንደሆነና ብዙ ግዜ ሊገድሉት እየሞከሩ አልተሳካላቸውም። ዲፕ-ስቴት ወገኖች በዓለም ጦርነቶች እንዲነሱና ብዙ ህዝብ እንዲያልቅ ከፍተኛ ፋልጎታቸው ነው።አሜሪካንን ከሩሲያና ቻይና ጋር ለማጋጨት የማይሞክሩት ነገር የለም። ሆኖም የአሜሪካው ፕሬዚደንት የራሳቸውን የግል የሰለላ ድርጅት ስላለው የቀድሞው የአሜሪካ ስለላ ድርጅት የሚፈልገውን ሁሉ የማድረግ አቅም የለውም።ይህም ፕሬዚደንቱ እስካሁን ለመኖራቸው አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያና አሜሪካ መንግስት ግንኙነት ከዚህ በፊት የነበሩት የአሜሪካ መንግስታት ከቡሽ ጀምሮ፣ ክሊንተንና ኦባማ ዓይነት ግንኙነት ከወያኔ መንግስት ጋር የነበረው ዓይነት ግንኙነት አይኖረውም። ምክንያቱም የወያኔ መንግስት በቅርቡም ሆነ ከዚያ በፊት የብዙ ኢትዮጵያውያን ደም በእጁ አለበት።በኢትዮጵያውያን ላይ የወያኔ መንግስት ላደረሳቸው ኢ-ስብዓዊ ድርጊቶች ለፍርድ የሚቀርብበት ሁኔታ የሚመቻችበትን ሁኔታ የአሁኑ የአሜሪካ መንግስት ፍላጎት እንዴሚሆን ተስፋ ይደረጋል። በአሜሪካም ሆነ በሌሎች አገሮች የኢትዮጵያን ገንዘብ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ዘርፈው ባንክ ሂሳብ በመክፈት ያስቀመጡትም ከተጠያቂነት የሚያድናቸው ሁኔታ አይኖርም።የህዝቡ ትግል ቀጥሎ ህዝቡ የሚፈልገውን ሲስተም ለመገንባት የሚችልበት ሁኔታ ከበፊቱ ለኢትዮጵያውያን ባሁኑ ወቅት የተሻለ ይመስላል። የወያኔ መንግስትና ኢትዮጵያ በወያኔው የከለላ ስም ኢሕአዴግ ወይም በግልጹ ወያኔ የብዙ ፓርቲዎች ሲስተም አለ ለማለት ዓላማ በማድረግ ለ 27 ዓመታት ኢሕአዴግ የሚለውን ሶስት የወያኔ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ተቅዋማት ፈጥሮ፣ ለራሱ ጉዳይ በደንብ ተጠቅሞበታል።እነዚህም የኦሮሞ፣ የደቡና የአማራ የወያኔ አገልጋይ ተቅዋማት ናቸው።እነዚህ ተቅዋማት በራሳቸው እራሳቸውን ችለው እንዲያስቡ ሳይሆኑ የወያኔ መንግስት የገደል ማሚቱ በመሆን አገልግለዋል።ከተወሰነ ግዜ በኋላ በአማራና በኦሮም ሕዝብ ግፉ ያንገፈገፋቸው ወጣቶች ፍርሃትን እርግፍ አድርገው፣ ደረታቸውን ለወያኔ አግአዚ ጦር በመስጠት ትግሉን አፋፍመውታል። ይህም ለወያኔ መንግስት ከዚህ በፊት እንደነበረው ሕዝብን እያጭበረበረና እያስፈራራ አገዛዙን መቀጠል አልቻለም። የለማና ዓቢይ ብቅ ማለት ከወያኔ ተቅዋማት አንዱ የነበረው ኦህዴድ ውስጥ በኦሮሞ ወጣቶች ላይ ይወሰዱ የነበሩትን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ዝም ብሎ ማለፍና እንደ ኦህዴድ አመራር መቀጠል የሚቻልበት ሁኔታ አለነበረም። የኦህዴድ አመራር እቶ ለማና ዶር ዓቢይ ከዚያ በፊት ባልተከሰተ ሁኔታ ችግሮቹን በግልጽ ማውጣትና ህዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የቄሮ፣ ፋኖና መርዛ የሕዝብ ትግሎች በየቦታው እየተቀጣጠሉ መሄዳቸው ግድ ሆኗል።ኦህዴድ „የመደብ ጭቆና እንጂ የብሄር ጭቆና የለም።"የሚል የወያኔን ፍልስፍና በቂጡ ቁጭ አድርጎታል።ለማና ዓቢይ የኢትዮጵያን አንድነት በመቀበል መሪ የሆኑ ጽንሳ ሃሳቦችን በቀጣይነት አሰጋብተዋል።

የአማራውና የኦሮም ሕዝብ አንድም ሁለትም የሆኑና በመከባበር አብረው ለበጎ ነግሮች የሚሰሩ መሆናቸውን ግንኙነታቸውን በማጠናከር፣ ወያኔ የፈጠረውን ደንቃራ ፈንግለው ጥለውታል። በኢሕአዴግ አሰራር አንድ ሰው ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን የሚያስችለው የድርጅቱ ሊቀ መንበርና የፓርላማ ተመራጭ መሆን እንዳለበት ነው። ይህንንም ለማሟላት ኦህዴድ ውስጥ ሊቀ መንበር የነበሩት እቶ ለማ ቦታውን ለቅቀው ዶር ዓቢይ እንዲመረጡ በማድረግ ፣ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ዝግጅቱን ፈጽመዋል። የቄሮ፣ ፋኖና ዘርማ ትግልና መስዋዕትነት ቄሮ፣ ፋኖና ዘርማ በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ ህዝባዊ ትግሉን በተገቢው መልክ በማፋፋም ድርሻቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ ነው። የወጣቶች ትግል አድማዎችን በማቀናጀት በኩል በጣም ውጤታማ እንደሆኑ ነው።ትግሉ የኢትዮጵይ ሕዝብ መብቶች የሚከበርበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እስከሚፈጠር ድረስ የሚቀጥል እንጂ፣ የብዙ ታጋይ ኢትዮጵያውያንን መስዋዕትነት በከንቱ የሚያስቀር አይሆንም።የወያኔ መንግስት በህዝብ ትግል ወድቆ ሰላምና ዴሞክራሲ በተግባራ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እውን እንዲሆን ነው።ከዚህ ሌላ መሃከለኛ መንግድ የለም። የአዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሚና ምን ሊሆን ይችላል? የአዲሱ የወያኔ ጠቅላይ ሚንስቴር ሚና የወያኔ መንግስት አገልጋይ፣ የወንጀለኞች አስጠባቂ፣ የዘራፊዎች አጋር፣ የኢ-ስበዓዊ እርምጃዎቹ አስፈጻሚ፣. . . ወዘተ ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆንና የሕዝቡን መሰረታዊ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች በተግባራ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የወያኔ ወንጀለኞች ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ ማመቻቸት ነው። የወያኔን መንግስት ለፍርድ ለማቅርብ ሆነ ሌሎች ሕዝቡ የሚፈልጋቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎችን እንዲመለሱለት የኢትዮጵያ ጦር አዛዡን፣ የጸጥታ ሃላፊውን፣ የፖሊስ ሃላፊውንና ሌሎችን የወያኔ ወንጀለኞች በሃላፊነት ከተቀመጡበት ማንሳትና በቁጥጥር ስር የሚውሉትን ማዋልና ለፍርድ ማቅረብ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራዊ ለማድረግ የኦህዴድና የብአዴን ትግሉን የሚደግፉ ሃይሎች ወታደሩንና ጸጥታውን በጋር ሊቆጣጠሩ ይገባል።በተለይም ወታደር ውስጥ ያሉት የሁለቱ ድርጅት ወታደሮችና የጸጥታ ሰዎች ትግሉን ሕዝቡ ወደሚፈልገው አቅጣጫ ለመምራት የሚንቀሳቀሱትን ሃይሎች ወያኔ ለማደናቀፍ ሲሞክር ዞርበል የሚል ሃይል በተጨባጭ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ የሚቀጥሉት እርምጃዎቹ ሁሉንም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅደመ ሁኔታዎች መፍታት፣ የአስቸኳይ አዋጁን ዛሬውኑ መሻር፣ የሚዲያ ተቅዋማትን ለህዝብ ክፍት ማድረግና የወያኔ ካድሬ የነበሩትን ማባረር ነው። „ህውሓት ቢዳከምም መከላከያው ውስጥ የበላይነቱ እንዳለ ነው። በደህንነቱም እንደዚያው። እነዚህን ሁለት ቁልፍ የስልጣን ማስጠበቂያ ተቋማትን እንዴት ከህወሓቶች እጅ ፈልቅቆ መውሰድ ይቻላል? እስከ አሁን ምንም ምልክት የለም። እነዶ/ር አብይ ውስጥ ለውስጥ ስራ ሰርተው ከሆነ እሰየው ነው። ህወሓቶች በመከላከያና በደህንነቱ ላይ የበላይነታቸው ከተገፈፈ ጨዋታው እንደሚያበቃ ያውቁታል። ያንን በመቃብራቸው ላይ ካልሆነ በቀር የሚፈቅዱት እንደማይሆን ይታመናል፡፡ ይህ ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ነው።" የሚለውን እኔም እጋራለሁ። የአማራው የወያኔ ድርጅት ብአዴንና የኦሮሞው የወያኔ ድርጅት ደኢህዴን አብረው በግልጽ ወጥተው ቢስሩ፣ ለትግሉ መፋጠን ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ እንደ አባ ዱላና በረከት ስምዖን የወያኔ ሆዳሞችን በመነጠል የሚሰራ ስራ ሊሆን ይገዋል።በወንጀል ውስጥ ያልተቸማለቁና በህዝብ ላይ ግፍ ያልፈጸሙትን ከሁለቱም ድርጅቶች ማሰባሰብና ማጠናከር ያስፈልጋል። ሙስና የኢትዮጵያን ምጣኔ

ሃብታዊ፣ማህበራዊና መንግስታዊ ድርጅቶች ሁሉ የጎዳ በመሆኑ በሙስና የተተበተቡ ሁሉ ለፍርድ የማቅረብ ሥራ መስራት የትግራይ ሕዝብ ከህወሓት ይልቅ ኢትዮጵያ እንደምታዋጣ በማሳመን ህወሓት የትግራይ ሕዝብ ዋስትና አለመሆኑን ማሳየት፣ ጠንካራና ታማኝ የምርጫ ቦርድ መመስረት ቅድሚያ ቢኖራቸው ማለፊያ ነው። አህዴድና ብአዴን አቶ ለማ መገርሳ ኦህዴድ ትግሉን በድል ለማጠናቀቅ የሚያስችል ብስለት አለው ።ከገፈኛው ወያኔ ጋር ብዙ ዘመናት የኖረ በመሆኑም ወያኔ ያለበትን ደካማ ጎንና አሁንም ያለዉን የጭንቀት ሁኔታ ጠንቅቆ ያዉቃ። ይህም ግንዛቤያቸዉ ነዉ ከሕዝቡ ትግል ጋር ተዳምሮ እዚህ ያደረሳቸዉ። ይህም ግንዛቤዉ ህወሓትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያስወግዱበት ዘንድ ያስችላል። ይህን ኦህዴድና የብአዴን ተራማጆች ከሕዝባቸዉ ጋር የበለጠ ለመናበብ ከሞከሩበትና መለስተኛና ከፍተኛ የክልሉ መሪዎቻቸዉ የስልጣናቸዉ ባለቤት ማድረግ ከቻሉ፤ ቄሮና ፋኖ እንዲኖር ከፈቀዱና መዋቅራቸው እንዲጠነክር ከተንቀሳቀሱ፣ በኢትዮጲያ ሕዝብ ልብ ዉስጥ ከሞተ የሰነባበተዉን ህወሓትን መመከት ብቻ ሳይሆን መቅበር ይችላሉ። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጀቶች ወደ ኢትዮጵያ የማስገባት ሂደትን በደንብ ልንመረምር እንደሚያስፈልግና፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጀቶች ስም ብዙ የውጭ አገሮች ሰላዮች ወይም የሰላይ ድርጅቶች መረጃ አቀባዮች ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ያስቻላል። ከዚህ ይልቅ ኢትዮጵያውያን ለሆኑ የአገር ውስጥ መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶችን ገንዘብና ቁሳቁሶችን በመላክ እንዲረዱ ማድረጉ የተሻለ ነው። አዲስ የሽግግር መንግስት መፍጠር አዲስ የሽግግር መንግስት በአንድ አገር ሲፈጠር ከውጪ አገሮች ምንም ያልሰሩና የወጪ ሃይሎች የገደል ማሚቱዎች በፖለቲካ ድርጅትነት ስም ወደ ኢትዮጵያ ለመግባትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሌላ የመከራ ዘመን መስዋዕት የሚያስደርጉ አሉ። በአጭሩ ከውጭ የሚመጣ የፖለቲካ ድርጅት ነን ባይ ወደ ኢትዮጵያ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ባይገቡ የተሻለ ነው።ከዚህ ይልቅ አገር ውስጥ በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ ካሉና የሽግግር መንግስቱ አገር ውስጥ ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሆኖ፣ እነዚህም ቢያንስ በአገር ውስጥ እንቃቃሴያቸው እውቅና ያላቸውና ከተፈጠሩ አምስት ዓመት እድሜና ቢያንስ 5000 ደጋፊዎች ያላቸው እንዲሆኑ ቢደረግ ጥሩ ነው። ጠቅላይ ሚንስትር ዶር ዓቢይ አህመድ ከወያኔ አሻጥር እንዴት ሊያመልጡ ይችላሉ? ጠቅላይ ሚንስትሩ የተመረጡት በኢሕአዴግ አባላት ነው።ይህም የብአዴን 45 ድምጽ፣ የኦህዴድ 45 ድምጽና 18 ድምጽ ከሌሎቹ በማግኘት በ 108 ድምጽ ድጋፍ እንደተመረጡ ነው።ወያኔ ወይም ሕወሓት የሚባለው ድርጅት ዛሬም ነጻ አውጪ ድርጅት ነኝ እያለን ነው። ጠቅላይ ሚንስትሩ የማንም የገደል ማሚቱ መሆን እንደማይፈልጉ መግለጻቸው ይነገራል።በአሁኑ ሰዓት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ደህንነት የሚጠብቁት ወያኔዎች በመሆናቸው፣ በፈለጉት ግዜ ዶር ዓቢይን የተለያዩ ተንኮሎችን ጠንሰሰው ሊገድሏቸው ወይም ሊያስገድሏቸው ይችላሉ። ሌላው ለጠቀላይ ሚኒስትሩ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታቸውን በመሸብረክ ለምሳሌ የመገንጠል ጥያቄ እንዲያነሱ በማበረታታት፣ ወይም ሌሎች ተንኮሎችን ሊጠነስሱ ይችላሉ። የወጭ አገር ሃይሎች ምክር ለኢትዮጵያ ብዙም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ምክንያቱም እነርሱ የራሳቸውን ሰላዮች ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቅዋማትን ኢትዮጵያ ውስጥ በማስገባት፣ የራሳቸውን ታዛዥ አሽከር የሚፈልጉ ናቸው።ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን መተባበርና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ መፍትሔ የሚመጣበትን ሁኔታ እውን ለማድረግ በቅንነት መንቀሳቀስ ይኖርብናል። አንድ ሰው „ዶር ዓቢይ፣ በቅርጫት ውስጥ ያለ እርግብ ይመስላል ማለት ነው። እርግቧ ወይ አትበር፣ ወይ አትራመድ በቅርጫቱ ውስጥ

ተወስና ለአጭር ግዜ፣ አሳሪዋ እስከሚያባርራት ወይም በጩኸቷ ተናዶ እስከሚያስወግዳት ድረስ በተሰጣት ቦታ ትኖራለች ማለት ነው።" ሲል የዶር ዓቢይ በወያኔ ቁጥጥር ስር መሆናቸውን ገልጿል። አስቸኳይ እርምጃዎች በአፋጣኝ መውሰድ እጅግ አስፈላጊነት

1ኛ. በቅድሚያ ከማንኛውም ሌሎች እርምጃዎች በፊት ጠቅላይ ሚንስትሩ የጦር ሃይል አዛዥነቱን በሕጉ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

2ኛ. የአሁኑን የወያኒ ጄኔራል የጦር አዛዡን በወንጀል የሚጠየቅ በመሆኑ ከስልጣኑ በማውረድ ሰራዊቱ የሚፈልገውን ሌላ ጄኔራል ከወያኔ ወንጀለኞች ውጪ መሾምና ለሕዝብ ማሳወቅ፣ ይህም በዘር ላይ የተመሰረተ ሊሆን ፈጽሞ አይገባውም።

3ኛ. የደህንነት ሚኒስቴር ሃላፊ የነበረውን አቶ ጌታቸው አሰፋን ለብዙ ወንጀሎች ተጠያቂ በመሆኑ ከስልጣኑ በማውረድ የብአዴን መሪ አቶ ገዱን መሾምና ለሕዝብ ማሳወቅ፣

4ኛ. የፖሊሲ አዛዡን የብዙ ወንጀሎች ተጠያቂ በመሆኑ፣ ከስልጣኑ እንዲወርድና ሌላ በፖሊሶች የሚደገፍና በችሎታው የሚተማመን ሰው መሾም ነው።

5ኛ. የወያኔ ድርጅት ብቻ ሳይሆን የሌሎች ድርጅቶች ባለስልጣናት በወንጀለኛነት የሚታወቁትን ሁሉንም ከስልጣናቸው መሻርና ለፍርድ ማቅረብ ነው።

6ኛ. የኦህዴድና የብአዴን ድርጅቶች ራሳቸውን ከወያኔ ወንጀለኞች ጋር የሚሞዳሞዱትን በመነጠል፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህይወት በወያኔ ወንጀለኞች አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፣ አሰፈላጊው ጥበቃ ከወያኔ ሰዎች ውጪ እንዲሆንና ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ መቻላቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

7ኛ. የቁሮ፣ ፋኖና ዘርማ ትግል በቋሚነት መሰረታዊ ለውጥ ኢትዮጵያዊ ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ መቀጠሉ በጣም ጠቃሚ ነው።

8ኛ. አገር ውስጥ ያሉትን ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋብዞ በማነጋገር፣ መፍትሄዎችን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉት ችግሮች እንዲያቀርቡ ማድረጉ ጠቃሚ ነው። እነዚህ በተወሰኑ ግዜያት በአፋጣኝ ተግባራዊ ማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከቻሉ፣ ሌሎችን አስፈላጊና ቀላል እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ አመቺ ይሆናል።

ከተንሳይት በቃና

6.4.2018